## ፲፫

ስድስተኛው ሕዋ አካል አሥር ጊዜ ይሰፋል። እጅግ በጣም ትላልቅ መጻሕፍት የሚጽፉ አዛውንት ሰው መኖሪያ ነው።

- ታዳጊውን ልዑል ሲያዩ «ወይ ጉድ! አገር አሳሽ» አሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው።

ታዳጊው ልዑል አጠረጴዛው ላይ ተቀመጠና አንድ አፍታ እፎይ አለ። እስካሁንም ጉዞ በዝቶበታል።

- ከየት ነው የምትመጣው? አሉት አዛውንቱ።

- ይኸ ወፍራም መጽሐፍ ምንድነው? አላቸው ታዳጊው ልዑል። እዚህ ምን ያደርጋሉ?

- የገጸ ምድር ባለሙያ ነኝ አሉት አዛውንቱ።

- የገጸ ምድር ባለሙያ ምንድነው?

- እሱማ ባሕሮች፣ ወንዞች፣ ከተማዎች፣ ተራራዎች፣ በረሃዎች የሚገኙበትን ቦታ የሚያውቅ ሊቅ ነው።

- ይኸ በእውነቱ ትኩረት የሚጋብዝ ነገር ነው፣ አለ ታዳጊው ልዑል። ሙያ ማለት ይኸ ነው አለና የገጸ ምድር ባለሙያውን ሕዋ አካል በዓይኑ ቃኘ። ይኸን የመሰለ ግርማ ያለው ሕዋ እስከ ዛሬ ገጥሞት አያውቅም።

- የርስዎ ሕዋ በጣም ያምራል። ውቅያኖሶች አሉበት?

- እኔ ምን አውቄ አሉ የገጸ ምድሩ አዋቂ።

- እንዴ! (ታዳጊው ልዑል ቅር ተሰኝቷል)። ተራራዎችስ?

- እኔ ምን አውቄ አሉ የገጸ ምድሩ አዋቂ።

- ከተማዎች፣ ወንዞች፣ በረሃዎችሳ?

- እነሱንም በፍጹም አላውቅም አሉ የገጸ ምድር አዋቂው።



- የገጸ ምድር ሊቅ እኮ ነዎት!

- ልክ ነው:: አሉ አዋቂው፣ ነገር ግን አገር አሳሽ አይደለሁም:: የአገር አሳሾች እጥረት አለብኝ:: እየዞረ ከተሞች ወንዞች ተራራዎች ባሕሮች ውቅያኖሶች በረሃዎች የሚቈጥረው የገጸ ምድር አዋቂ አይደለም:: የገጸ ምድር አዋቂ ታላቅ ሰው ስለሆነ ለዙረት ጊዜ የለውም:: ከጽሕፈት ቤቱ አይወጣም:: ግን አገር አሳሾችን እየተቀበለ ያነጋግራል:: እየመረመረ ትውስታቸውን ይመዘግባል:: ከነሱ መካከል ያንዱ ትዝታ ጠቃሚ ሲመስለው የገጸ ምድሩ ሊቅ የግለሰቡን ሥነ ምግባር ያስመረምራል::

- ምክንያቱ ምንድነው?

- አንድ አገር አሳሽ ሐሰተኛ ነገር የተናገረ እንደሆነ በገጸ ምድር መጻሕፍት ላይ የሚያስከትለው አደጋ ከፍተኛ ነው:: መጠጥ የሚያበዛም አገር አሳሽ ያው ነው::

- ለምን አለ ታዳጊው ልዑል::

- ስካራሞች ነገሩ ሁሉ እጥፍ እየሆነ ስለሚታያቸው ነው:: ስለሆነም የገጸ ምድሩ ባለሙያ አንድ ተራራ ብቻ ያለበትን ቦታ ሁለት ተራራዎች ብሎ ይመዘግባል::

- አገር አሳሽ የሆነ ብቃት የሌለው አንድ ግለሰብ አውቃለሁ::

- ይሆናል:: እንግዲህ የአሳሹ ሥነ ምግባር ጥሩ መሆኑ ሲታመንበት ስለ ግኝቱ ይመረመራል::

- እቦታው ድረስ ተሂዶ ይታያል?

- የለም:: ያማ ነገሩን በጣም ውስብስብ ያደርገዋል:: አገር አሳሹ ማስረጃ እንዲያቀርብ ይገደዳል:: ለምሳሌ ግኝቱ የሚመለከተው አንድ ትልቅ ተራራ ከሆነ ታላላቅ ድንጋዮች ማምጣት አለበት::

የገጸ ምድሩ ሊቅ በድንገት ስሜቱ ተቀሰቀሰ::

- ለካ አንተም የመጣኸው ከሩቅ ነው! አገር አሳሽ ነህ! እስኪ ያንተ ሕዋ አካል ምን እንደሚመስል ንገረኝ!

የገጸ ምድሩም ሊቅ መዝገቡን ዘረጋ እርሳሱንም ቀረጸ:: የአግር አሳሾች ገለጻ በፊት በእርሳስ ነው የሚጻፈው:: በቀለም የሚጻፈው ማስታወሻ አሳሹ መረጃዎቹን እስኪያቀርብ ድረስ ይቆያል::

- እህ? ሲል የገጸ ምድሩ ሊቅ ጠየቀ::

- አይ! የኔው እንኳ ብዙም ትኩረት አይስብም፣ በጣም አነስተኛ ነው:: ሦስት እሳተ ገሞራዎች አሉኝ:: ሁለቱ አልጠፉም፣ አንዱ ከስሟል:: ግን ማን ያውቃል::

- ማን ያውቃል አለ የገጸ ምድሩ ሊቅ::

- አንዲት አበባም አለችኝ::

- አበባ እንመዘግብም አለ የገጸ ምድሩ ሊቅ::

- ምነዋ! በውበት ከሁሉም የምትበልጠው እሷ ነች::

- አበባዎች አላፊ ጠፊ ስለሆኑ፣ «አበባ አለው ገለባ» ይባላል::

- «አላፊ ጠፊ» ማለት ትርጉሙ ምንድነው?

- የገጸ ምድር ሥነ ጽሑፎች፣ አለ ሊቁ ከመጻሕፍት ሁሉ የበለጡ ብርቅዬ መጻሕፍት ናቸው:: ዘመን መቼም አይሽራቸውም:: ተራራ ቦታ ለወጠ ሲባል ተሰምቶም አይታወቅ:: ውቅያኖስ ውኃው ደርቆ ባዶውን ቀረ ሲባል ተሰምቶም አይታወቅ:: እኛ የምንጽፈው የማያልፈውን ነገር ነው::

- ታዳጊው ልዑል የሊቁን ንግግር አቋርጦ የከሰሙ እሳተ ገሞራዎች መልሰው ሊነቁ ይችላሉ አለ:: «አላፊ ጠፊ» ማለት ትርጉሙ ምንድነው?

- እሳተ ገሞራዎች ይጥፉም ይቀስቀሱ ለኛ ለውጥ የለውም አለ የገጸ ምድሩ ሊቅ:: ለኛ ዋናው ነገር ተራራው ነው:: የማይለወጥ ስለሆነ...::

- ዕድሜ ልኩን አንድ ጊዜ ጥያቄ ካቀረበ መልሱን ሳያገኝ የማይለቀው ታዳጊ ልዑል «አላፊ ጠፊ» ማለት ምን ማለት ነው? ብሎ በድጋሚ ጠየቀ::

- «በቅርቡ የመጥፋት አደጋ የሚያሠጋው» ማለት ነው::

- የኔ አበባ በቅርቡ የመጥፋት አደጋ ያስፈራዋል?

- እንዴ!

የኔ አበባ ጠፊ ረጋፊ ሆና መከላከያዋ አራት እሾኾች ብቻ ናቸው:: በዚህ ላይ ብቻዋን ትቻት ነው ካገሬ የወጣሁት::

መጀመሪያ ተጸጸተ፣ በኋላ ግን ራሱን አጽናንቶ፣

- ምን እንድጐበኝ ይመክሩኛል? ብሎ ጠየቀ::

- ምድር የተሰኘችውን ሕዋ አካል ብሎ መለሰለት፣ የገጹ ምድሩ ሊቅ። ዝናዋ ትልቅ ነው…።

ታዳጊው ልዑል አበባይቱን እያሰበ ወደዚያው ተጓዘ።



# ፲፮

ስለዚህ ሰባተኛው ሕዋ አካል ምድር ናት።

ምድር ተራ ሕዋ አካል አይደለችም! አንድ መቶ አሥራ አንድ ነገሥታት ይገኙባታል (ያውም ጥቋቁሮቹ ነገሥታት ሳይቈጠሩ)፣ ሰባት ሺህ የገጸ ምድር ሊቃውንት፣ ዘጠኝ መቶ ሺህ ነጋዴዎች፣ ሰባት ሚሊዮን ተኩል ሰካራሞች፣ ሦስት መቶ አሥራ አንድ ሚሊዮን ጕረኞች፣ ማለትም በጠቅላላው ሁለት ቢሊዮን ትልልቅ ሰዎች አሉ ማለት ነው።

መጠኗ ምን እንደሚያህል ለመግለጽ ያህል ኤሌክትሪክ ከመምጣቱ በፊት በስድስቱ አኅጕራት አራት መቶ ስድሳ ሁለት ሺህ አምስት መቶ አሥራ አንድ የመንገድ መብራት አብሪዎች ሠራዊት መቀለብ ያስፈልግ ነበር። ራቅ ብለው ሲያዩት ተግ ብሎ አንጸባራቂ ነበር። የሠራዊቱ እንቅስቃሴ እንደ ኦፔራ ውዝዋዜ ሥርዓት የያዘ ነበር። መጀመሪያ የኒው ዚላንድና የአውስትራሊያ አብሪዎች ይመጣሉ። መብራቶቻቸውን ያበሩና ሄደው ይተኛሉ። ቀጥለውም የቻይናና የሳይቤሪያ አብዎች ተራቸውን ውዘዋዜውን ይያያዛሉ። ከዚያ ወደ ጓዳ ገብተው ይሠወራሉ። ያን ጊዜ የራሻና የሕንድ መብራት አብሪዎች ተራ ይደርሳል። የአፍሪቃና የአውሮጳ ይቀጥላል። ከዚያ የደቡብ አሜሪካ፣ ብሎም የሰሜን አሜሪካ። ወደ መድረክ ሲወጡ ተራቸውን በፍጹም አያሳስቱም፤ ትርዒቱ አስገራሚ ነበር። ሰሜናዊ ዋልታ ላይ ብቻውን የቆመውን መብራት የሚያበራውና ደቡባዊ ዋልታ ላይ ብቻውን የቆመውን መብራት የሚያበራ የሥራ ባልደረባው እነዚህ ሁለቱ ብቻ የቦዘኔና የግድየለሽ ኑሮ ይኖሩ ነበር። ሥራ የሚሠሩት በዓመት ሁለት ጊዜ ነው።

## ፲፯

ንግግር እናሳምር ሲሉ በመጠኑ መዋሸት ይመጣል። ስለ መብራት አብሪዎቹ ስተርክላችሁ በጣም ሐቀኛ አልነበርኩም። መሬታችንን የማያውቁትን ሰዎች የተሳሳት ግንዛቤ በማግኘት አደጋ ላይ ልጥላቸው እችላለሁ። ምድር ላይ ሰዎች የያዙት ቦታ እጅግ አነስተኛ ነው። ምድር ላይ የሚኖሩት ሁለት ቢሊዮን ሰዎች ሕዝባዊ ስበሰባ ላይ እንደሚደረገው ትንሽ ተቀራርበው ቢቆሙ ሃያ ማይል በሃያ ማይል ስፋት ያለው አደባባይ ይበቃቸዋል። የሰውን ልጅ ዘር በአነስተኛ የፓሲፊክ ደሴት ውስጥ አጨናንቆ ማስፈር ይቻላል።

ትልልቆቹ ሰዎች እርግጥ አያምኑህም። ብዙ ቦታ የሚይዙ እንደ ወርካ የተንሰራፉ ይመስላቸዋል። ስለዚህ ሂሳቡን እንዲያወጡ ምከራቸው። አኃዞች በጣም ስለሚወዱ ስሌቱን አይጠሉትም። እርስዎ ግን በዚህ አታካች ሥራ ጊዜዎን አያጥፉ። ፋይዳ የለውም። እኔን ያምኑኛል።

ታዳጊው ልዑል መሬት ሲነካ ማንንም ባለማግኘቱ ተደነቀ። ተሳስቶ ሌላ ሕዋ ላይ ያረፈ መስሎት ፍራት ፍራት ማለት ሲጀምረው ጨረቃ የሚመስል ቀለበት አሸዋ ላይ ተላወሰ።

- ታዳጊው ልዑል እንዲያው በመላ «እንዴት አመሹ» አለ።

- እባቡም «እንደምን አመሹ» ብሎ መለሰ።

- ማን እሚባለው ሕዋ ላይ ነው እግር የጣለኝ? ብሎ ጠየቀ ታዳጊው ልዑል።

- «ምድር ላይ አፍሪካ ውስጥ» ብሎ መለሰለት እባቡ።

- እንዴ! ... ታዲያ እመሬት ላይ ሰውም የለ?

- ይኸ በረሃ ነው። በረሃ ውስጥ ማንም የለ። መሬት ሰፊ ናት፣ አለ እባቡ።

ታዳጊው ልዑል ድንጋይ ላይ ተቀመጠና ዓይኑን ወደ ሰማይ አንሥቶ፣

- ከዋክብት የሚያበሩት እያንዳንዱ ሰው አንድ ቀን ኮከቡን ፈልጎ ለማግኘት እንዲችል ይሆናል። የኔን ሕዋ አካል እያት። ልክ አናታችን ላይ ናት ... አቤት ርቀቷ!

- ታምራለች አለ እባቡ። እዚህ ምን ልታረግ መጣህ?

- ከአንዲት አበባ ጋር ችግር ገጥሞኛል አለ ታዳጊው ልዑል።

- ነው! አለ እባቡ።

እናም ሁለቱም ዝም አሉ።

- ታዳጊው ልዑል መልሶ፣ «ታዲያ ሰዎቹ የሉም?» አለ። በረሃ ውስጥ በመጠኑም ቢሆን ብቸኝነት አለ...።

- ብቸኝነቱስ በሰዎችም መካከል አይጠፋም አለ እባቡ።

ታዳጊው ልዑል ሲመለከተው ቆየና፣

«አስገራሚ አውሬ ነህ፤ ቅጥነትህ ጣት የሚያህል»... አለው።

- ኃያልነቴ ግን ከንጉሥ ጣት ይበልጣል አለ እባቡ።

ታዳጊው ልዑል ፈገግ አለ፣

- በጣም ኃያል አይደለህም ... እግር እንኳን የለህ! ... ከቦታ ቦታ መጓጓዝ አትችል ...

- ከመርከብ የበለጠ ሩቅ ልወስድህ እችላለሁ አለ፣ እባቡ።

በታዳጊው ልዑል ቁርጭምጭሚት ላይ እንደ ወርቅ አምባር ተጠመለለ፣

- ቀጥሎም «የምነካውን ሰው ወደመጣበት ወደ አፈርነቱ እመልሰዋለሁ» አለ። አንተ ግን ንጹሕ ነህ፤ የመጣኸውም ከኮከብ ነው...።

ታዳጊው ልዑል ምንም አልመለሰ።

- እንዳንተ ያለ ደካማ በዚህች በጥቁር ድንጋይ መሬት ላይ መገኘቱ ያሳዝነኛል። የሕዋ አካልህ በጣም ከናፈቀህ አንድ ቀን ልረዳህ እችላለሁ።



በመጨረሻ ታዳጊው ልዑል «አስገራሚ አውሬ ነህ፣ ቅጥነትህ ጣት
የሚያህል... አለው::

- በጣም ገብቶኛልኮ፣ ግን ለምንድነው ንግግርህ ሁልጊዜ ምስጢር አዘል እንቆቅልሽ የሚሆንብኝ?

- እንቆቅልሹን ሁሉ እፈታዋለሁ፣ አለ እባቡ።

ሁለቱም ዝም አሉ።

## ፲፰

ታዳጊው ልዑል በረሃውን ሲያቋርጥ ከአንዲት አበባ በስተቀር ማንም አልገጠመው። ሦስት ቅንጣት ብቻ ያላት አበባ፣ አልባሌ አበባ ...

- ጤና ይስጥልኝ አለ ታዳጊው ልዑል።

- ጤና ይስጥልኝ አለች አበባይቱ።

- ሰዎቹ የት ነው ያሉት? ብሎ ታዳጊው ልዑል በጨዋ ደንብ ጠየቀ።

- አበባዋ አንድ ቀን ሲራራ ነጋዴዎች ሲያልፉ አይቼ ነበር፣

- ሰዎች? ስድስት ሰባት የሚሆኑ ያሉ ይመስለኛል። ካየኋቸው ዓመት አልፈዋል። የት እንደሚገኙ ግን ፈጽሞ አይታወቅም። ንፋስ ይዟቸው ይዞራል። እነሱም ሥራቢሶች በመሆናቸው ብዙ ቅሬታ ይሰማቸዋል።

- ደህና ሰንብቺ አለ ታዳጊው ልዑል።

- ደህና ሁን አለችው አበባይቱ።

# ፲፱

ታዳጊው ልዑል አንድ ታላቅ ተራራ ላይ ወጣ። ከዚህ ቀደም የሚያውቀው እነዚያን ጉልበቱ የሚደርሱ ሦስት እሳተ ገሞራዎች ብቻ ነው። የጠፋውን እሳተ ገሞራ እንደ በርጩማ ይቀመጥበት ነበር። «ይኸን ከሚያህል ተራራ ላይ ከወጣሁ ሕዋ አካሉ በሙሉ ከነሰዎቹ ወለል ብሎ ይታየኛል» … ብሎ አሰበ። ነገር ግን ጫፉቸው ሹል ከሆነ ሾጣጣ አለቶች በስተቀር ሌላ ምንም አልታየውም።

- እንዲያው በመላ እንዴት ዋላችሁ ሲል።

- የገደል ማሚቶው እንዴት ዋላችሁ … እንዴት ዋላችሁ … እንዴት ዋላችሁ … ብሎ መለሰ፣ የገደል ማሚቶው።

- ማ ልበል? አለ፣



ታዳጊው ልዑል።

- ማ ልበል?... ማ ልበል?... ማ ልበል? ብሎ መለሰ የገደል ማሚቶው።

«ምን ዓይነት ሕዋ አካል ነው! ብሎ አሰበ። ከመድረቁ መሾሉ፣ በዚያ ላይ አሸቦ መምሰሉ። ሰዎቹም ምናብ ያንሳቸዋል። የተባለውን ነው የሚያስተጋቡት። እኔ አገር አንዲት አበባ ነበረችኝ፣ ሁልጊዜ በንግግር ማንም የማይቀድማት ...»

# ፳

ታዳጊው ልዑል በአሸዋው በአረሁ በበረዶው መካከል ለረዥም ጊዜ ከተጓዘ በኋላ በመጨረሻ አንድ መንገድ ገጠመው። መንገድ ሁሉ ሄዶ ሄዶ ሰዎቹ ወዳሉበት ነው የሚደርሰው።

- እንዴት ዋላችሁ አለ።

ጽጌሬዳዎች ያበቡበት አትክልት ነበር።

- እንዴት ዋሉ፣ አሉ አበቦቹ።

ታዳጊው ልዑል ትክ ብሎ አያቸው። ሁሉም መልካቸው የሱኑ አበባ ይመስላል።


- እጅግ ደነቀውና «ማናችሁ?» አላቸው።


«እኛ ጽጌሬዳዎች ነን» አሉት።

- «ይገርማል» አለ ታዳጊው ልዑል። ...

ከዚያም ጥልቅ ሐዘን ተሰማው። ያቺ የሱ አበባ «እኔ በፍጥረተ ዓለም ከሚገኙት አበባዎች ሁሉ በመልክ የሚመስለኝ የለም» ብላ ያወራችለት ትዝ ብሎት ነው። አሁን አንድ መስክ ውስጥ ብቻ እነሆ አምስቱም ሺህ አበቦች መልካቸው አንድ ነው!

«ይኸንን ብታይ በጣም ይከፋት ነበር ... በኃይል ሳልይዟት ሐፍረቷን ለመሸፈን በሳል ለመሞት የደረሰች ትመስል ነበር።





እኔም የማስታምማት መምሰል ይኖርብኝ ነበር፣ አለበለዚያማ እኔንም ለማሳፈር ስትል የምሯን ሞታ ታርፈዋለች።

ሐሳቡን በመቀጠል «ብርቅ አበባ አለችኝ ብዬ በሀብቴ ስመካ ተራ ጽጌረዳ ሆና ተገኘች። አበባዬና ቁመታቸው ከጉልበቴ የማይደርስ ሦስት እሳተ ገሞራዎች ያውም አንደኛው ምናልባት ለዘለቄታው የከሰመ እነዚህን ይዤ ትልቅ ልዑል እሆናለሁ ማለት አያዋጣኝም...» አለና እመስኩ ላይ ተኝቶ አለቀሰ።


## ፳፩

ቀበሮው ብቅ ያለው በዚህ ጊዜ ነው።

- ጤና ይስጥልኝ አለ ቀበሮ።

- ታዳጊው ልዑል በጨዋ ደንብ «አሜን፣ ጤና ይስጥልኝ» አለና ዘወር ቢል ምንም የለ።

- እዚህ እቱፋ ዛፍ ሥር ነኝ ሲል ድምፁን አሰማ...።
- ማነህ? አለ ታዳጊው ልዑል።
መልክህ ማማሩ...።
- ቀበሮው ሲመልስ «ቀበሮ ነኝ» አለ።
- ና አብረን እንጫወት ብሎ ጋበዘው ታዳጊው ልዑል። እኔ በጣም አዝኛለሁ።...
-ካንተ ጋር መጫወት አልችልም አለው ቀበሮው።እኔ የአውሬነት ባሕርይ እንዲለቀኝ አልምዶ ገራም አላደረጉኝም።
ታዳጊው ልዑል አሰበበትና፣
- «አልምደው» ማለት ምን ማለት ነው? አለው።
- አንተ የዚህ አገር ሰው አይደለህም፣ አለው ቀበሮ፣ ምን እየፈለግህ ነው?
- እኔ እምፈልገው ሰዎችን ነው። አለ ታዳጊው ልዑል። «አልምደው» ማለት ምን ማለት ነው?
- ሰዎች ጠመንጃ አላቸው፣ አደንም ይወጣሉ። ችግር ነው! ዶሮም ያረባሉ። ሌላ ሙያ የላቸውም። ዶሮ ነው የምትፈልገው?
- የለም አለ ታዳጊው ልዑል። እኔ የምፈልገው ወዳጅ የሚሆነኝ



ነው:: «አልምደው» ማለት ምን ማለት ነው?

- በጣም የተረሳ ነገር ነው አለ ቀበሮው:: «ትስስር መፍጠር» ማለት ነው...::

- ትስስር መፍጠር?

- ነውና አለ ቀበሮው:: ሳይህ ገና ታዳጊ ነህ:: በመቶ ሺህ ከሚቈጠሩ ታዳጊ ልጆች በምንም አትለይም:: ለኔም አታስፈልገኝም:: እኔም አላስፈልግህ:: እኔ ላንተ ከመቶ ሺህ ቀበሮዎች ያልተለየሁ ቀበሮ ነኝ:: ካለመድከኝ ግን እኔና አንተ እንፈላለጋለን:: አንተ ለኔ በዚህ ዓለም ውስጥ የብቻዬ ትሆናለህ:: እኔም ላንተ በዚህ ዓለም የብቻህ እሆናለሁ::...

- እየገባኝ ነው አለ ታዳጊው ልዑል:: አንድ አበባ አለች... ያለመደችን ይመስለኛል...

- ሊሆን ይችላል አለ ቀበሮው:: ዓለም ላይ ብዙ ዓይነት ነገር ይታያል...

- አይ ዓለም ላይ አይደለም አለ ታዳጊው ልዑል::

ቀበሮው ግራ ገባው፣

- ሌላ ሕዋ አካል ላይ ነው አልከኝ?

- አዎ::

- እዚያ ሕዋ አካል ላይ አዳኞች አሉ?

- የሉም::

- ወይ ታሪክ! ዶሮዎችስ?

- የሉም::

- መቸም አሟልቶ አይሰጥ አለ ቀበሮ በትካዜ::

ቀበሮ ወደ ቀድሞ ሐሳቡ ተመለሰና፣

- የኔ አኗኗር ያሰለቻል:: እኔ ዶሮ አድናለው፣ ሰዎች እኔን ያድናሉ:: ዶሮ ከዶሮ ይመሳሰላል፣ ሰውም ከሰው:: ስለዚህም ነው ስልችት የሚለኝ:: አንተ ለመድከኝ ግን ፀሐይ ወጣልኝ ማለት ነው:: የምሰማው የኮቴ ድምፅ ከሌሎቹ ሁሉ የተለየ ይሆናል ማለት ነው:: ሌሎቹ በአረማመዶች ጒድጓድ ያስገቡኛል::

ያንተ ግን እንደ ሙዚቃ ከጕሬ ያስወጣኛል:: ከዚህ በስተቀር እስቲ ተመልከት እዚያ ማዶ የስንዴ ማሳዎች ይታዩሃል? እኔ ዳቦ አልበላም:: ስንዴ ለኔ ጥቅም የለውም:: የስንዴ ማሳዎች ላይ ምንም ትዝ የሚለኝ ነገር የለም:: የሚያሳዝን ነገር ነው! ጸጕርህ ወርቅማ ነው:: ለማዳ ካደረግኸኝ ሁሉ ነገር ግሩም ይሆናል:: ስንዴው ሲደርስና ወርቅ ሲመስል አንተን ያስታውሰኛል:: እስንዴውም ላይ የሚነፍሰውን ነፋስ ድምፁን መውደድ እጀምራለሁ:: ...

ቀበሮው ዝም አለና ታዳጊውን ልዑል በረጅሙ አስተዋለና፣

- እባክህ ... ለማዳ አድርገኝ አለው!

- «ማልመድ ምን ገዶ» ብሎ መለሰለት ታዳጊው ልዑል፤ «ጊዜ ያጥረኛል እንጂ» ወዳጆች ፈልጌ ማበጀት አለብኝ:: ሌላም ለማወቅ የምፈልገው ብዙ ነገር አለ::

- «ማወቅ የሚቻለው ያለመዱትን ነገር ብቻ ነው» አለ ቀበሮው:: ሰዎች ምንም ነገር ለማወቅ ጊዜ የላቸውም:: እነጋዴዎች ዘንድ የሚገዙት ሁሉ ሥራው ያለቀለት ነገር ነው:: ወዳጅ የሚሸጥ ነጋዴ ስለሌለ ሰዎች ወዳጅ ይቸግሯቸዋል:: ወዳጅ ካማረህ እኔን አልምደኝ!

- ምን ይሻላል? አለ ታዳጊው ልዑል::

- ትእግስተኛ መሆን ነው ብሎ ቀበሮው መለሰለት::

- መጀመሪያ እንዲያው ዝም ብለህ እሣሩ ላይ ከኔ ራቅ ብለህ ቁጭ ትላለህ:: እኔ በጐን አይሃለሁ፣ አንተ ግን ምንም አትልም:: ነገር ሲበዛ ጠብ ያበቅላል:: በየቀኑ ግን ቀረብ እያልክ መቀመጥ ነው...

በማግሥቱ ታዳጊው ልዑል ተመልሶ መጣ::

- በዚያው ሰዓት ብትመጣ ይሻል ነበር አለው ቀበሮ:: ለምሳሌ ከቀትር በኋላ በአሥር ሰዓት ብትመጣ እኔ ደስታ የሚሰማኝ ገና ከዘጠኝ ጀምሮ ይሆናል:: ሰዓቱ በገፋ መጠን ደስታዬ እየላቀ ይሄዳል:: አሥር ሰዓት ሲሞላ መወራጨትና መስጋት እጀምራለሁ፣

የደስታው ዋጋ ገባኝ ማለት ነው! በፈለግኸው ሰዓት ከመጣህ ግን ልቤን አለባብሼ የምቆይበት ሰዓት ይጠፋኛል። ለሁሉም ሥርዓት ያሻዋል።

- ሥርዓት ማለት ምን ማለት ነው? አለ ታዳጊው ልዑል።

- እየተረሱ ከሄዱት ነገሮች አንዱ ነው አለ ቀበሮው። አንዱን ቀን ከሌላው፣ አንዷን ሰዓት ከሌሎቹ የተለየች የሚያደርጋት ሥርዓት ነው። ለምሳሌ እኔን የሚያድኑቱ ግለሰቦች የራሳቸው ሥርዓት አላቸው። ሐሙስ ሐሙስ ከመንደሩ ኮረዳዎች ጋር ይደንሳሉ። ስለሆነም ሐሙስ የቀን ቅዱስ ነው! እስከ ወይኑ ተክል ድረስ እንሸራሸራለሁ። አዳኞቹ በፈለጉት ቀን ቢደንሱ ኖሮ ቀኖቹ ሁሉ እየተመሳሰሉ እረፍት አጣ ነበር።

እንዲሁ እያለ ታዳጊው ልዑል ቀበሮውን ለማዳ አደረገው። መሄጃው ሰዓት ሲደርስ፡

- አይ! አለ ቀበሮው ... ማልቀሴ ነው።

- በገዛ እጅህ አለው ታዳጊው ልዑል፣ እኔ ክፉ ነገር አልተመኘሁልህ፣ ለማዳ እንዳደርግህ የፈለግኸው ራስህ ነህ።...

- እርግጥ ነው አለ ቀበሮው።

- ስታለቅስ ልትኖር ነው! አለው ታዳጊው ልዑል።


- መጠርጠሩ! ብሎ መለሰለት ቀበሮው።

- ብታለቅስ ምን ታገኛለህ!

- የስንዴው ማሳ ኅብረ ቀለም እስካለ ምን ገዶ።

ቀጥሎም፣





ለምሳሌ ከቀትር በኋላ በአሥር ሰዓት
ስትመጣ እኔ ደስታው የሚሰማኝ ገና
ከዘጠኝ ሰዓት ጀምሮ ነው።

- በል ሂድና ጽጌረዳዎቹን ጠይቃቸው:: ያንተ አበባ በዓለም ላይ ብርቅዬ መሆኗን ትገነዘበዋለህ:: ስትመለስ ትሰናበተኛለህ:: ያን ጊዜ አንድ ምስጢር በስጦታ መልክ እነግርሃለሁ::

ታዳጊው ልዑል ጽጌረዳዎቹን ሊጠይቅ ሄደ::

- በፍጹም የኔን ጽጌረዳ አትመስሉም፣ ገና ለምንም አትበቁም አላቸው:: ማንም ለማዳ አላደረጋችሁም፣ እናንተም ማንንም አላለመዳችሁ:: የኔ ቀበሮ በነበረበት ሁኔታ ናችሁ:: እሱ በመቶ ሺህ ከሚቈጠሩ ሌሎች ቀበሮዎች በምኑም አይለይም ነበር:: ግን ወዳጄ አድርጌው አሁን በዓለም ላይ አንድና ብቸኛ ብርቅ ቀበሮ ሆኗል::

ጽጌረዳዎቹም በጣም ተሸማቀቁ::

- ንግግሩን በመቀጠል «ታምራላችሁ ግን ባዶ ናችሁ» አላቸው:: ለናንተ ብሎ የሚሞት የለም:: እርግጥ ለተራ መንገደኛ የኔይቱ አበባ እናንተን ትመስለው ይሆናል:: እሷ ግን አንድ ብቻዋን ከናንተ ሁሉ ትበልጣለች፣ ምክንያቱም ውኃ ያጠጣኋት እሷን ስለሆነ ነው:: ክዳን ያበጀሁላት እሷ ነች:: ግርዶሽ ሠርቼ ያስጠለልኳትም እሷን ነው:: አባ ጨጓሬዋን (ሁለት ሦስት ለቢራቢሮነት አስተርፌ) የገደልኩላት እሷ ነች:: ቅሬታዋን ስታሰማኝ ወይም ስትጐርርብኝ የሰማኋት፣ አልፎ አልፎም ዝም ስትል ያየኋት እሷ ነች:: የኔ ጽጌረዳ ስለ ሆነች::

ከዚያም ወደ ቀበሮው ተመለሰ፣

- ደህና ሁኑ አለ ...

- ደህና ሁን አለው ቀበሮው:: የማካፍልህ ምስጢር እነሆ፤

- በስሜት ካላዩት አይጠራም:: ፍሬ ነገር ለዓይን እንግዳ ነው::

- ታዳጊው ልዑል እንዳይረሳው በድጋሚ፣ «ፍሬ ነገር ለዓይን እንግዳ ነው» አለ::

- ያንተ ጽጌረዳ ይህን ያህል ዋጋ ያገኘችው አንተ ባጠፋህላት ጊዜ ምክንያት ነው::



እመስኩ ላይ ተኝቶ
አለቀሰ።

- «እኔ ለጽጌረዳዬ ያጠፋሁላት ጊዜ ነው» አለ ታዳጊው ልዑል እንዳይረሳው::
- ሰዎች ይኸንን እውነት ረስተውታል አለ ቀበሮው:: አንተ ግን መርሳት የለብህም:: ላለመድከው ነገር የዘለዓለም ኃላፊነት አለብህ:: ለጽጌረዳህ ተጠያቂው አንተ ነህ...
- ለጽጌረዳዬ ተጠያቂው እኔ ነኝ አለ ታዳጊው ልዑል እንዳይረሳው::

# ፳፪

- እንዴት ዋላችሁ! አለ ታዳጊው ልዑል::
- ይመስገነው! አለ የሐዲድ መሥመር ተቈጣጣሪው::
- እዚህ ምን ያደርጋሉ? አለው ታዳጊው ልዑል::
- መሥመር ተቈጣጣሪው፣ «መንገደኞቹን በአንዳንድ ሺህ እየደለደልኩ ነው:: የሚያጓጉዙአቸውን ባቡሮች አንዱን ወደ ቀኝ አንዱን ወደ ግራ እያሰማራሁ ነው::»
በዚህ ጊዜ አንድ ባለመብራት ፈጣን ባቡር እንደ ነጐድጓድ እያጕረመረመ ሲያልፍ የተቈጣጣሪውን ሰንተርያ አንቀጠቀጠው::
- ምን አጣደፋቸው አለ ታዳጊው ልዑል:: ምንድነው የሚፈልጉት?
- ባቡር ነጂው ራሱ ለምን እንደሚጣደፍ አያውቀውም አለ መሥመር ተቈጣጣሪው::
አሁንም ሌላ ባለመብራት ፈጣን ባቡር በተቃራኒው አቅጣጫ አጕረመረመ::
- የቅድሞቹ መመለሳቸው ነው? አለ ታዳጊው ልዑል::

- እነዚያ አይደሉም አለ ተቈጣጣሪው። ቅያሪ ነው።

- የነበሩበትን ጠልተውት ነው?

- ሰው ባለበት ቦታ መች ተደስቶ ያውቃል አለ መሥመር ተቈጣጣሪው። እነደገና ሦስተኛ ፊጣን ባለመብራት ባቡር ነጐድጓዱን አሰማ።

- የመጀመሪያዎቹን ተጓዦች እያሳደዱ ነው? አለ ታዳጊው ልዑል።

- ምንም የሚያሳድዱት ነገር የለም አለ መስመር ተቈጣጣሪው። እዚያ ውስጥ እያንቀላፉ ወይም እያዛጋቸው ነው። ልጆቹ ብቻ ናቸው አፍንጫቸውን እመስተዋቱ ላይ የሚደፈጥጡት።

- የሚፈልጉትን የሚያውቁ ልጆቹ ብቻ ናቸው አለ ታዳጊው ልዑል። በጨርቅ ለተሠራች አሻንጉሊት ጊዜያቸውን ያባክናሉ፣ ለነሱ ትልቅ ነገር ነች፣ የወሰዱባቸው እንደ ሆን ያለቅሳሉ...።

- ዕድለኞች አለ መሥመር ተቈጣጣሪው።



## ፳፫

- እንዴት ዋላችሁ? አለ ታዳጊው ልዑል።
- ይመስገነው አለ ነጋዴው።

ውኃ ጥም የሚያረኩ ጥራት ያላቸው እንክብሎች ነጋዴ ነው። ውኃ እንዳይጠማ በሳምንት አንዷን መዋጥ ብቻ ነው።

- ይህን ለምን ትሸጠዋለህ? አለ ታዳጊው ልዑል።
- ነጋዴው ሲመልስ፣ «በከፍተኛ ደረጃ ጊዜ ስለሚቈጥብ ነው» አለ። ባለሙያዎች ያካሄዱት ጥናት አለ። በሳምንት ሃምሳ ሦስት ደቂቃ የጊዜ ቍጠባ ለማድረግ ያስችላል።
- ሃምሳ ሦስቱን ደቂቃ ምን ምን ያደርጉበታል?
- እንደ ፈለጉ ይጠቀሙበታል...።
- ታዳጊው ልዑል በሆዱ፣ «እኔ የማጠፋው ሃምሳ ሦስት ደቂቃ ቢኖረኝ ቀስ እያልኩ ምንጭ ወዳለበት አዘግም ነበር» አለ።

## ፳፬

በረሃ ውስጥ አደጋ ከደረሰብኝ ሳምንት ሲሆነው፣ የነጋዴውን ታሪክ ያዳመጥኩት የውኃ ስንቄን መጨረሻ ጠብታ እየጠጣሁ ነበር።

- እሺ! አልሁት ታዳጊውን ልዑል። «ያወሳሃቸው ትዝታዎች በጣም ደስ ይላሉ። እኔ ግን ኤሮፕላኔን ገና አልጠገንኩም፣ የምጠጣውም የለኝ፣ እናም እኔም እንዳንተ ምንጭ ወዳለበት ቀስ እያልኩ ባዘግም ደስ ይለኝ ነበር!»
- ወዳጄ ቀበሮ... አለኝ ታዳጊው ልዑል።
- ወዳጄዋ ቁም ነገሩ ስለ ቀበሮው አይደለም!

- ለምን?

- በውኃ ጥም መሞታችን ስለሆነ...።

አስተሳሰቤ አልገባውም ነበርና፣ ሲመልስልኝ እንዲህ አለ፣

- መሞታችን ቢሆን አንድ ወዳጄን ማትረፉ አይከፋም።

እኔ የቀበሮ ወዳጅ በማግኘቴ ደስ ብሎኛል...።

በልቤ «ይኽ ልጅ ሊደርስበት የሚችለውን አደጋ አልተገነዘበውም ብዬ አሰብኩ። እሱ አይርበው አይጠማው። ትንሽ ፀሐይ ካገኘ ይበቃዋል...።

እሱ ግን አየት አደረገኝና ለሐሳቤ መልስ ሲሰጥ፣

- እኔም ውኃ ጠማኝ የውኃ ጉድጓድ እንፈልግ አለኝ...።

ስልችት አለኝና «ጭው ያለ በረሃ ውስጥ በዳበሳ የውኃ ጉድጓድ መፈለግ ምን ትርጉም አለው። ያም ሆኖ ጉዞውን ተያያዝነው።

ለሰዓታት አንድ ቃል ሳይወጣን ከተጓዝን በኋላ መሸና ከዋክብቱ ማብራት ጀመሩ። በውኃ ጥሙ ምክንያት ትንሽ ስላተኩሰኝ ከዋክብቱ የሚታዩኝ እንደ ሕልም ነበር። የታዳጊውም ልዑል ንግግር በምናቤ ውስጥ ይጉላላ ነበር።

- አንተም ውኃ ጠምቶሃል ብዬ ጠየቅሁት።

መልስ አልሰጠኝም። እንዲያው በቀላሉ፣

- ውኃም ለልብ ጥሩ ሊሆን ይችላል አለኝ...።

መልሱ አልገባኝም ነበርና ዝም አልኩ...። ጥያቄ ባበዛበት ጥሩ እንደማይሆን አውቅ ነበር።

ደክሞት ነበር። ቁጭ አለ። እኔም አጠገቡ ተቀመጥኩ። ጸጥ ብሎ ትንሽ ቆየና፣

- ከዋክብቱ የሚያምሩት በአንዲት በማትታይ አበባ ምክንያት ነው... አለ፣ ንግግሩን በመቀጠል፣

- እንዴ! ብዬ መለስኩለትና በጨረቃ ወገግታ የአሸዋውን ስንበር በጥሞና አስተውል ጀመር።

- በረሃ ውብ ነው አለ። በንግግሩ ላይ በማከል። ጥርጥር

የለውም:: እኔ ቀድሞውንም በረሃ እወድ ነበር:: አሸዋ ሰንበር ላይ መቀመጥ ነው:: ምንም የሚታይ የለም:: ምንም አይሰማም:: ያም ሆኖ በጸጥታ የሚያንጸባርቅ ነበር አለ...::

- ለበረሃ መልክ የሚሰጠው ባልታወቀ ቦታ ምንጭ ተሸሽጎ መገኘቱ ነው ... አለ ታዳጊው ልዑል::

የአሸዋ ምስጢራዊ ነጸብራቅ መኖሩን በድንገት መገንዘቤ ደነቀኝ:: ልጅ ሆኜ የምኖርበት ቤት የቆየ ስለ ነበረ ቅርስ ተቀብሮበታል የሚል አፈ ታሪክ ይነገራል:: እርግጥ ቅርሱን ያገኘ የለም፣ የፈለገም ሰው መኖሩ ያጠራጥራል:: ለቤቱ ግን አድናቆት አበርክቶለታል:: ቤቴ በማኅፀኗ ምስጢር ይዛለች...::


- አዎ! አልኩት ታዳጊውን ልዑል:: «ቤትም ይሁን ከዋክብት ወይም በረሃ ውበት የሚሰጣቸው ምን እንደሆነ በዓይን ማየት አይቻልም!

- ከቀበሮዬ ጋር መስማማትህ ደስ ብሎኛል::

ታዳጊው ልዑል እንቅልፉ መጥቶ ስለ ነበረ ታቀፍኩትና ጉዞዬን ቀጠልኩ:: ስሜት አደረብኝ:: ተሰባሪ ሀብት የተሸከምኩ ይመስለኛል:: እምድር ላይ ከዚህ የበለጠ ተሰባሪ ነገር ያለ አይመስለኝም:: በጨረቃ ብርሃን ነጭ ግንባሩን፣ የተከደኑ ዓይኖቹን፣ በነፋስ የሚውለበለበውን የጸጕሩን ቀንጮ እያየሁ «ይኸ የማየው ሁሉ ቅርፊት ነው:: ዋናው ለዓይን አይታይም» እል ነበር...

ከንፈሮቹ ተገልጠው በከፊል ፈገግ ሲል «እንቅልፍ ለያዘው ልዑል ይህን ያህል ስሜት ያደረብኝ ለአንዲት አበባ የሚያሳየው ታማኝነት፣ በተኛበትም ቢሆን እንደ መቅረዝ ብርሃን በልቡ የሚያበራው የጽጌረዳይቱ ሥዕል ነው::» ... ብዬም በልቤ አሰብኩ:: ከዚህም የበለጠ ተሰባሪ እንደሚሆን ግምት ነበረኝ:: መብራትን ተጠንቀቆ መንከባከብ ያሻል፣ ነፋስ ሽው ቢል ያጠፋዋልና...::

ሳዘግም አድሬ ጐሕ ሲቀድ የውኃ ጉድጓዱን አገኘሁት...::



ሣቀ፣ ገመዱን ነካው፣
መዘውሩን ሞከረው::

# ፳፫

- ሰዎች፣ አለ ታዳጊው ልዑል፣ በየጅረቱ እየዘለሉ ይገባሉ ግን የሚፈልጉትን ማወቅ ይሳናቸዋል። በዚህ ጊዜ ይቅበጠበጣሉ ይሽከረከራሉ...

ቀጥሎም፣

- ዋጋ የለውም ... አለ።

ያገኘነው ጉድጓድ የሰሐራን ጉድጓዶች አይመስልም። የሰሐራ ጕድጓድ በቀላሉ የተቈፈረ አሸዋ ነው። ይኸኛው ግን የመንደር ጕድጓድ ይመስላል። ነገር ግን ባካባቢው መንደር ስላልነበረ በሕልሜ ነው በእውኔ ብዬ ጠረጠርኩ።

- «ይገርማል» አልኩት ታዳጊውን ልዑል ዝግጅቱ የተሟላ ነው፣ መዘውሩም ባልዲውም ገመዱም አለ...።

ሣቀና ገመዱን ነካው፣ መዘውሩን ሞከረው። ነፋስ ለረዥም ጊዜ ሳይነሣ ቀርቶ እንዳልተንቀሳቀሰች የጣራ ሽክርክሪት መዘውሩ ሲጢጥ ሲጢጥ አለ።

- ይሰማሃል አለ ታዳጊው ልዑል ጉድጓዱን ከተኛበት ስንቀሰቅሰው ጊዜ መዝፈን ጀመረ ...

እንዲቸገር አልፈለግሁም ነበርና፡

- እስቲ ለኔ ተውልኝ ላንተ በጣም ይከብድሃል አልኩት። ቀስ እያልኩ ባልዲውን ጕድጓዱ ገደፍ ድረስ ስቤ አወጣሁና እገደፉ ላይ አመቻችቼ አስቀመጥኩት። የመዘውሩ ዝማሬ ሳያቋርጥ የሚሰማኝ ይመስለኛል። በሚንቀጠቀጠው ውኃ ውስጥ ፀሐዩ ሲንቀጠቀጥ ይታየኛል።

-«የ ውኃ ጠጡኝ ጠጡኝ ይላል»... አለ ታዳጊው ልዑል።

እኔም ምን እንደ ፈለገ ገባኝ!

ባልዲውን እስከ ከንፈሩ ድረስ ከፍ አደረግሁለት። ዓይኑን

ጨፍኖ ጠጣ:: እንደ እርጎ አንጀቱን አራሰው:: ያ ውኃ ከምግብ የተለየ ነበር:: ከጨረቃ በታች ጉዞ፣ ልብ የሚያረካ በሕፃንነቴ ለልደት በዓል የሚመጣልኝን ስጦታ ነጸብራቅ የሚያጐናጽፉት የገና ዛፉ መብራት የመንፈቀ ሌሊቱ ማጎሌት የፈገግታዎቹ ልስላሴ ነበር::

- ታዳጊው ልዑል ሲመልስለት «ያንተ አገር ሰዎች አምስት ሺህ አበባዎች በአንድ ጓሮ ይተክላሉ...:: ያም ሆኖ ግን የሚፈልጉትን አያገኙበትም::

- እርግጥ የሚፈልጉት አያገኙትም ብዬ መለስኩለት ...

- ታዲያ እኮ የሚፈልጉት ነገር ባንዲት ጽጌረዳ ወይም ባንድ ጥርኝ ውኃ ሊገኝ ይችላል...

- እውነት ነው አልኩት::

ታዳጊው ልዑልም ሲመልስልኝ፣

- ዓይን ያያል እንጂ አያስተውልም:: መሻት በልብ ነው::

- ውኃዬን ጠጥቼ ትንፋሼ ተመልሷል:: ሲነጋጋ የአሸዋው ቀለም ማር ይመስላል:: ይህ ማር የመሰለ ቀለም እኔንም ያስደስተኛል:: ሐዘን ለምኔ?...::

- እንደገና አጠገቤ ተቀምጦ የነበረው ታዳጊው ልዑል ቀስ ብሎ፣ «የገባኸውን ቃል መጠበቅ አለብህ» አለኝ::

- ምን የገባሁት ቃል አለ?

- መች አጣኸው ... ለበጌ መሸለቢያ ... ለዚያች ለአበባ ኃላፊነት አለብኝ!

የሥዕል ንድፎቼን ከኪሴ አወጣሁ:: ታዳጊው ልዑል አይቶ ሣቀና፣

- ዋርካዎችህ ወደ ጐመንነት ይወስዳቸዋል...::

- ኧረ!

እኔ ያንን ያህል ስኩራባቸው!

- ቀበሮህ... ጆሮዎቹ ትንሽ ወደ ቀንድነት ይወስዳቸዋል... በዚህ ላይ በጣም ረዝመዋል!

አሁንም ሣቀ፣

- ጨከንከብኝ አንተዬ ከድፍን ዘንዶና ከክፍት ዘንዶ በስተቀር ሌላ ነገር መሣል አላውቅም ነበር።

- አይ አትጨነቅ ልጆች አያመልጣቸውም።

በዚህ ጊዜ መሽለቢያውን ሥዬ ስሰጠው አንጀቴ ቡጭ ቡጭ አለ።

- እኔ እማላውቀው ነገር አቅደሃል...።

እሱ ግን አልመለሰልኝም።

- ታውቃለህ መሬት እምትባለው ሕዋ አካል ላይ ከወደቅሁ ነገ አንድ ዓመቴ መሆኑ ነው ... አለኝ።

ደግሞ በዝምታ ትንሽ ቆየና፣

- እዚህ አካባቢ ነው የወደቅሁት አለኝ።

ከዚያም ፊቱ በርበሬ መሰለ።

ለምን እንደሆነ አላውቅም እንደ ገና ግራ የሚያጋባ ሐዘን ተሰማኝ። ሆኖም አንድ ጥያቄ በሐሳቤ መጣብኝ።

- እንግዲያውማ ያለፈው ሳምንት ጧት ስንተዋወቅ ሰው ካለበት አካባቢ 1852 ኪሎሜትር ርቀት ላይ ዝም ብለህ ብቻህን ትንሽራሽር የነበረው ያለ ምክንያት አልነበረም ማለት ነዋ? ወደ ወደቅህበት መመለስህ ነበር? አልኩት።

ታዳጊው ልዑል እንደ ገና ፊቱ ቀይ ሆነ።

እኔም ስፈራ ስቸር፣

- ዓመት የሞላህበትን ቀን ለማክበር ይሆን?... አልኩት።

ታዳጊው ልዑል አሁንም ቀይ ሆነ። ሲጠይቁት አይመልስም ነበር፣ ግን ቀይ መሆን ያው «አዎ» ማለት አይደለም እንዴ?

- ወይኔ አልኩት፣ ፍራት ፍራት አለኝ...።

እሱ ግን፣

- አሁን መሥራት አለብህ። ወደ መኪናህ ተመልሰህ መጓዝ አለብህ። እዚህ እጠብቅሃለሁ። ነገ ማታ ተመልሰህ ና...

እኔ ግን መንፈሴ አልተረጋጋም ነበር። የቀበሮው ነገር ትዝ

ይለኛል። መለማመድ ከመጣ ትንሽ ማልቀስ አይቀርም።...

# ፳፯

ከውኃ ጉድጓዱ አጠገብ የአሮጌ ካብ ፍርስራሽ ነበር። በማግሥቱ ማታ ከሥራዬ ስመለስ ታዳጊው ልዑል ሆዬ አፋፉ ላይ እግሮቹን አንጠልጥሎ እንደ ተቀመጠ ከሩቅ አየሁት። ሲነጋገርም ይሰማኛል፣

- «አታስታውስም? እንዴ ልክ እዚህ አልነበረም!» ይላል።

- አዎ፣ እዎ፣ ቀኑ ትክክል ነው፣ ቦታው ግን እዚህ አይደለም...።

ወደ ግንቡ ማምራቴን ቀጠልኩ። ማንም አይታየኝ፣ ሌላም ድምፅ አይሰማኝ። ታዳጊው ልዑል ግን አሁንም መልስ ሲሰጥ፣... እህሳ። አሸዋው ላይ የእግሬ ፈለግ የት እንደ ጀመረ ይታይሃል። እዚያ ላይ እኔን መጠበቅ ብቻ ነው። ዛሬ ሌሊት እደርሳለሁ።

እግንቡ አጠገብ ለመድረስ ሃያ ሜትር ነው የቀረኝ ግን አሁንም ቢሆን ማንም አይታየኝ።

ታዳጊው ልዑል አንድ አፍታ ዝም አለና ንግግሩን በመቀጠል፣

- መርዝህ ፍቱን ነው? ሥቃዩ እንደማይቆይብኝ እርግጠኛ ነህ አለው?

ቀጥ ብዬ ቆምኩ፣ ልቤ ትርትር አለ፣ አሁንም አልገባኝም።

- አሁን በል ወጊድልኝ ... ልውረድበት! አለው።

በዚህ ጊዜ እኔም ራሴ ወደ ግንቡ ሥር ዓይኔን ጣል ሳደርግ ወደ ኋላ ተፈናጠርኩ። መርዙ በሠላሳ ስከንድ ሰው የሚገድለው ዓይነት ቢጫ እባብ ታዳጊው ልዑል ላይ አንገቱን አስግጎላችኋል። ሽጉጤን ለማውጣት ኪሴን እየፈተሽኩ ወደ ፊት ሩጫዬን ስጀምር እባቡ እርምጃዬን ሰምቶ ኖሮ አሸዋው ላይ ሽለል አለና ፍልቅታውን እንዳቋረጠ ፏፏቴ ሰብሰብ ብሎ በአለቶቹ መካከል እየተቅጨለጨለ በእርጋታ ሹልክ ብሎ ሄደ።

ልክ እግንቡ ሥር ሲደርስ የኔ ታዳጊ ልዑል ፊቱ እንደ በረዶ ነጭ ሆኖ እክንዴ ላይ ውድቅ አለ።

- የምን ታሪክ አመጣህብኝ! ብለህ ብለህ ከአባቦች ጋር ማውራት ጀመርክ?

አውልቆት የማያውቀውን ወርቅማ ያንገት ልብስ ፈታሁለት፡፡ ጆሮግንዱን አራስኩለትና ውኃ አጠጣሁት፡፡ ከዚያ ምንም ልጠይቀው አልደፈርኩም፡፡ ትኩር ብሎ አየኝና አንገቴ ላይ ጥምጥም አለ፡፡ ልቡ ሲመታ በጥይት ቄስሎ እንደሚሞት የወፍ ልብ ትርታ ነበር፡፡ እንደዚህ አለኝ፣

- ለመኪናህ የሚያስፈልገውን ዕቃ ስላገኘህ ደስ ብሎኛል፡፡ እንግዲህ ወዳገርህ መሄድ ልትችል ነው...፡፡

- እንዴት አወቅህ!

እኔ የመጣሁት ሥራዬ ከምጠብቀው በላይ የተሳካልኝ መሆኑን ልነግረው ነበር!

ላቀረብኩለት ጥያቄ ምንም መልስ አልሰጠኝ፣ ግን በንግግሩ ላይ በማከል፣

- እኔም ዛሬ አገሬ እገባለሁ ... አለኝ፡፡

ከዚያም በትካዜ፣

ኋንተ አገር በጣም ይርቃል...፡፡ መንገዱም የበለጠ ያስቸግራል፡፡

አንድ በጣም ልዩ የሆነ ነገር በአእምሮው ውስጥ እንደሚጉላላ ተሰማኝ፡፡ እንደ ሕፃን ልጅ እቅፍ ሳደርገው ይገፍ ላስቀረው በማልችልበት ሁኔታ ቁልቁ ብሎ አዘቅት እንደሚወርድ ሰው ሲንሸራተት ይሰማኛል...፡፡

ኩስተር ብሎ ዓይኑን አሻግሮ ወርወር አደረገና፣

- በግህ አለኝ፡፡ የበጉም ሣጥን አለኝ፣ መሸለቢያውም አለኝ፡፡ ...

ፊቱ ፈገግ ቢልም ትካዜ ይታይበታል፡፡

ብዙ ቆየሁ፤ ቀስ እያለ ሰውነቱ ሲሞቅ ይሰማኛል፡፡

- ማሙዬ፣ ፍራት ይዞህ ነው...፡፡

ፍራትማ ይዞታል! ግን ቀስ ብሎ እየሣቀ፣

- ዛሬ ማታ የበለጠ የሚያስፈራኝ ... አለ፡፡



«አሁን በል ወጊድልኝ ...
ልውረድበት!» አለው።

ልመልሰው የማልችለው አደጋ እንደገና በሐሳቤ ግጥም አለብኝና ሰውነቴ በስሜት ቀዘዘ። ያንን ሣቁን ዳግመኛ መስማት አለመቻሌን ማሰቡ ብቻ የማልችለው ስሜት እንደሚያሳድርብኝ ገባኝ። ሣቁ ለኔ የምድረበዳ ምንጭ ነው።...

እሱ ግን፣

- ዛሬ ሌሊት ዓመት መሆኑ ነው። የኔ ኮከብ ልክ አምና እወደቅሁበት ቦታ አናቱ ላይ ትደርሳለች...

- ማሙዬ፣ ይኸ ሁሉ የእባብ የቀበሮና የኮከብ ታሪክ ቅዠት አይደለም? ...

- ለጥያቄዬ መልስ አልሰጠኝም ግን...

- አስፈላጊ ነገር በዓይን አይታይም... አለኝ።

- ነውና...።

- እንደ አበባይቱ ነው። ኮከብ ላይ ያለች አበባ ከወደድህ ሌሊት ጠፈሩን ቀና ብሎ ማየት ደስ ይላል። ከዋክብት ሁሉ በአበባ ተጊጠዋል።

- እኮ...።

- ውኃም ያው ነው። ያጠጣኸኝ ውኃ በመዘውሩና በገመዱ ምክንያት እንደ ሙዚቃ ነው ... ትዝ እንደሚልህ ... ጣዕሙ ልዩ ነበር።

- መች አጠጣሁት? ...

- ሌሊት ከዋክብትን ተመልከት። የኔይቱ ኮከብ በጣም ስለምታንስ አገሬም ጠባብ ስለሆነ ከዚህ ላሳይህ አልችልም። እንዲያውም ይኸው ይሻላል። የኔ ኮከብ ላንተ ከከዋክብቱ መካከል አንዷ ነች። ስለዚህ ከዋክብቶቹን ሁሉ ስታያቸው ደስ ይልሃል። ሁሉም ወዳጆችህ ይሆናሉ። በዚህ ላይ አንድ የምሰጥህ ስጦታ አለ...።

እንደ ገና ሣቀ።

- አይ ማሞ፣ የእኔ ማሙዬ ፣ ይኸ አሣሣቅህ ደስ ሲለኝ!

- ይኸውልህ የኔ ስጦታ እሱው ነው ... እንደ ውኃው ነው ...

- ምን ለማለት ፈልገህ ነው?

- ከዋክብት ለሰዎች ሁሉ አንድ አይደሉም:: አንዳንዶች የሚጓዙ ሰዎች ኮከቦችን መሪዎቻቸው ያደርጓቸዋል:: ሌሎች ከብርሃን ብልጭታ ለይተው አያዩአቸውም:: በእውቀት ለላቁቱ ሰዎች ከዋክብት የጥያቄ ምልክቶች ናቸው:: እኔ ለተገናኘሁት ነጋዴ ወርቅ ናቸው:: ግን እነዚያ ከዋክብት አንድ ቃል አይወጣቸውም:: ላንተ የሚሰጡህ ከዋክብት ግን ለማንም ተሰጥተው የማያውቁ ናቸው::...

- ምን ማለት ፈልገህ ነው?

- ሰማዩን ሌሊት ስትመለከት እኔ ባንዱ ኮከብ ላይ ስለምኖር፣ እዚያ ላይ ሆኜ እሥቃለሁና አንተ ኮከቦች ሁሉ የሣቁ መስሎ ነው የሚሰማህ:: ያንተ ድርሻዎች የሚሥቁ ከዋክብት ይሆናሉ::

አሁንም ሣቀ::

- ስትጽናና (መጽናናት አይቀርምና) አውቀው ነበር ስትል ደስ ይልሃል:: ለዘለዓለሙ ወዳጄ ነው:: ከኔ ጋር ስትሆን ሣቅ ሣቅ ይልሃል:: አንዳንድ ጊዜም ዝም ብለህ መስኮትህን ትከፍታለህ፣ ለደስታ ያህል... ሰማይ ሰማይ እያየህም ስትስቅ ወዳጆችህ በጣም ይገርማቸዋል:: ያን ጊዜ፣ «አዎ ከዋክብት ሁልጊዜ ያሥቁኛል!» ብለህ ትመልስላቸዋለህ:: እነሱም አብዷል ብለው ያምናሉ:: አጉል ቀልድ ቀለድኩብህ ማለት ነው::

አሁንም ሣቀ::

- በከዋክብት ፋንታ አንድ አገር ሙሉ መሣቅ የሚያውቁ ቅጭልጭሎች የሰጠሁህ ያህል ነው...::

ይህን ብሎ እንደ ገና ሣቀ:: ወዲያው ኮስተር አለና፣

- ዛሬ ሌሊት... ገባህ... አትምጣ...::

- ጥዬህ አልሄድም::

- እንደ ታመመ ሰው ያደርገኛል... በመጠኑም እንደ ሞተ ሰው እሆናለሁ:: ይኸው ነው:: ይኸንን ለማየት አትምጣ ግድ የለም...

- ጥዬህ አልሄድም።
ግን ስጋት ገብቶታል።
- ይኸንን የምልህ ... በአባቡም ምክንያት ነው። እንዳይነድፍህ ያስፈልጋል... አባብ ክፉ ነው። ነደፋ ሊያስደስተው ይችላል። ጥዬህ አልሄድም።
ሆኖም አንድ ነገር አረጋጋው።
- ሁለተኛ ጊዜ ሲነድፉ መርዝ የላቸውም...።
ያን ሌሊት ለመጓዝ ሲነሣ አላየሁትም። ድምፁን አጥፍቶ ነው የኰበለለው። ስደርስበት እርምጃውን ሳብ ሳብ የሚያደርገው በቊርጠኛነት ነበር። ንግግር ሳያበዛ ባጭሩ፣
- ታዲያስ ደረስክ ... አለኝ።
ከዚያም እጄን ያዘኝ። ግን ጭንቀቱን ቀጠለ፣
- ልክ አይደለህም። ታዝናለህ። የሞትሁ እመስላለሁ እንጂ የእውነት አልሞትም...።
እኔ ዝም።
- ይገባሃል። በጣም ሩቅ ነው። ይኸንን ሰውነቴን ይዤ መሄድ አልችልም። በጣም ይከብዳል።
- እኔ ዝም።
- አርጅቶ እንደ ተጣለ ቅርፊት ይሆናል። ያረጁ ቅርፊፊቶች አያሳዝኑም።
እኔ ዝም።
ትንሽ ተስፋ ቈረጠ። ግን እንደ ገና አንሰራራና፣
- ጥሩ ይሆናል፣ ታውቃለህ። እኔም ከዋክብትን አያለሁ። ከዋክብቱ ሁሉ የዛገ መዘውር ያለባቸው ጕድጓዶች ይሆኑልኛል። ከዋክብቱ ሁሉ የምጠጣው ውኃ ያንቆረቁሩልኛል።...
እኔ ዝም።
- በጣም ነው ደስ የሚለው! አንተም አምስት መቶ ሚሊዮን ቅጭልጭሎች፣ እኔም አምስት መቶ ሚሊዮን ምንጮች ይኖሩናል።...




ከዚያም እሱም ዝም አለ፣ እንባ አንቆት ነበርና...።

- ያው ደረስን። ተወኝ አንድ እርምጃ ብቻዬን ልራመድ።

ፈርቶ ነበርና ቁጭ አለ።

ከዚያም እንዲህ አለኝ፣

- ታውቃለህ ... አበባዬ ... ኃላፊነት አለብኝ! በጣም ደካማ ነች! በዚህ ላይ የዋህ። ዓለምን ለመቋቋም ያላት መሣሪያ አራት የማይረቡ እሾኾች ብቻ ናቸው...።



መቆም ስለ ተሳነኝ ቁጭ አልኩ::
እሱም፣
- ይኸው... በቃ... አለ::
አሁንም ትንሽ አንገራገረና ከተቀመጠበት ተነሣ:: አንድ እርምጃ ተራመደ:: እኔ መነቃነቅ አልቻልኩም ነበር::
ቀጥ ብሎ ቆመ:: ጩኸት አላሰማም:: እንደሚገረሰስ ዛፍ ቀስ እያለ ወደቀ:: አሸዋ ላይ ስለ ነበረ ሲወድቅ ድምፁ እንኳን አልተሰማም::

## ፳፯

አሁንማ እንግዲህ ስድስት ዓመት ሆነው:: ይህንን ታሪክ ለማንም ነግሬ አላውቅም:: ያገኙኝ ጓደኞቼ በሕይወት ስላገኙኝ እጅግ ደስ አላቸው:: እኔ አዝኜ ነበር ግን «ድካሙ ነው»... አልኳቸው:: አሁን በመጠኑ ተጽናንቻለሁ:: ቢሆንም... በሙሉ አይደለም::
ግን ወደ ሕዋ አካሉ መመለሱን በእርግጥ አውቃለሁ፣ ምክንያቱም ሲነጋ፣ ሰውነቱን አላገኘሁትም:: ይህን ያህል ከባድ አካል አልነበረም ... ሌሊት ከዋክብትን ማዳመጥ ደስ ይለኛል:: ድምፃቸው እንደ አምስት መቶ ሚሊዮን ቅጭልጭሎች ነው...::
እዚህ ላይ አንድ ታይቶ የማይታወቅ ነገር ደረሰ:: ለታዳጊው ልዑል እሳልኩለት መሸለቢያ ላይ የጠፍሩን ሽምቀቆ መሣል ዘንግቻለሁ! እበጉ አፍ ላይ ሊያስረው በፍጹም አይችልም ማለት ነው:: «ሕዋ አካሉ ላይ ምን ተፈጥሮ ይሆን» እያልሁ ራሴን እጠይቅ ጀመር:: ምናልባት በጉ አበባይቱን በልቶ ይሆናል...::
ወዲያው ደግሞ፣ «አይ በፍጹም! ታዳጊው ልዑል ማታ ማታ አበባዋን የመስታወት ከዳን ይከድንባታል፤ በጉንም በሚገባ



እንደሚገረሰስ ዛፍ ቀስ እያለ ወደቀ።

ይጠብቀዋል...።» ይህንን ሳስብ ደስ ይለኛል። በዚህም ጊዜ ከዋክብቱ ሁሉ በቀስታ ይሥቃሉ።

አልፎ አልፎ በሆዴ ሳስብ፣ «አንዳንድ ቀን መዘናጋት አይቀርም። ያን ዕለት አለቀ ማለት ነው! ወይ አንድ ቀን መክደኛውን ይረሳል፤ ወይ በጉ ሌሊት ድምፁን አጥፍቶ ይወጣል...።» ያን ጊዜ ቅጭልጭሎቹ ሁሉ ድምፃቸው ወደ ለቅሶ ይለወጣል! ...

ይኸ በራሱ ምስጢር አዘል ነገር ነው። የት እንደ ሆነ ባልታወቀ ቦታ፣ አንድ የማናውቀው በግ አንድ ጽጌረዳ በልቷል ወይስ አልበላም የሚል ጥያቄ እስካልተነሣ ድረስ፣ ለናንተ ታዳጊውን ልዑል ለምትወዱትና ለኔም ጭምር፣ ፍጥረተ ዓለም ውስጥ ምንም ተመሳሳይ ነገር የለም ማለት ነው...።

ሰማዩን ተመልከቱ። «በጉ አበባይቱን በልቷል ወይስ አልበላትም?» ብላችሁ ራሳችሁን ጠይቁ። ሁሉም ነገር እንዴት እንደሚለወጥ ታያላችሁ።...

መቼም ነፍስ ካወቁት ግለሰቦች መካከል አንዱም ይህ ጉዳይ ምን ያህል ታላቅ ቁም ነገር ያለበት መሆኑን አይገነዘበውም!

ተፈጸመ

